# በኢትዮጵያ ፡ ቅዱስ ፡ ሲኖድ ።

## ለኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የተሰጠ ።

## ፪ ተ ኛ ፡ ሲ ኖ ዶ ስ ።

ተጎተመ ፡ ዝንቱ ፡ መጽሐፍ ፡ በጀወሮቱ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥቱ ፡ ለቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዘኢትዮጵያ ።

አ ፡ አ ፡ ኅዳር ፡ ፲፯ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፷፯ ፡ ዓ፡ ም፡

በትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት ታተመ ፲፯ ፻ ፵፭ ቀ፡ ፳፻፯ ብ፳፲

www.ethiopianorthodox.org

## በኢትዮጵያ ፡ ቅዱስ ፡ ሲኖዶ ።

## ለኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የተሰጠ ።

## ፬ ተ ኛ ፡ ሲ ኖ ዶ ስ ።

ተንትመ ፡ ገዝንቱ ፡ መጽሐፍ ፡ በጽወደት ፡ ዘመኑ ፡ መንግሥቱ ፡ ለቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዘኢትዮጵያ ።

አ ፡ አ ፡ ኅዳር ፡ ፲፯ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፵፯ ፡ ዓ፡ ም፡

በትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት ታተመ ፲፯ ፫ ፵፯ ቍ ፩ሺ፩ ብ፩ሺ

★ ዲያቆን ሰሎሞን ዮሐንስ ★
Dn Solomon Yohannes
0911 60113
0111/2 ...
www.ethiopianorthodox.org
www.ethiopianorthodox.org

በኢትዮጵያ ፡ ቅዱስ ፡ ሲኖድ ። ለኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክር

ስቲያን ፡ የተሰጠ ። ፪ተኛ ፡ ሲኖዶስ ።

## ፩ ኛ ፤

## ክርስትና ፡ ስለተነሱ ፡ ሰዎች ፡ መዝገብ ፡ አጻጻፍ ።

ሕፃንም ፡ ሆነ ፡ አዋቂ ፡ ክርስትና ፡ ሲነሳ ፡ የክርስትና ፡ ስሙና ፡ መጠሪያ ፡ ስሙ ፡ የአባቱና ፡ የናቱ ስም ፡ አገሩ ፡ በመዝገብ ፡ ሊጻፍ ፡ ይገባል ፡ የክርስቲያንነቱም ፡ መታወቂያ ፡ የምስክር ፡ ወረቀት ፡ ይሰጠዋል ፡ የመዝገቡም ፡ ስም ፡ መዝገበ ፡ ሃይማኖት ፡ ይባላል ።

ስለ ፡ ክርስትና ፡ መነሻም ፡ በረከት ፡ እቀበልበታለሁ ብሎ ፡ በፈቃዱ ፡ ከሚሰጠው ፡ በቀር ፡ በክርስትና ፡ ጊዜ ፡ ዋጋ ፡ መቀበል ፡ ክልክል ፡ ነው ።

## ፪ ኛ ፤

## ስለሞቱ ፡ ሰዎች ፡ መዝገብ ፡ አጻጻፍ ።

ሰው ፡ ሲሞት ፡ የራሱ ፡ ስም ፡ የተወለደበት ፡ አገር ፡ የአባትና ፡ የእናቱ ፡ ስም ፡ የአረፈበት ፡ አገር ፡ የነፍስ ፡ አባቱ ፡ ስም ፡ በመዝገብ ፡ ሊጻፍ ፡ ይገባል ፡ የመዝገቡም ፡ ስም ፡ መዝገበ ፡ ዕረፍት ፡ ይባላል ።

ይህም ፡ የሚጻፍበት ፤ የጽሕፈት ፡ መግረያና ፡ መዝገብ ፡ የቤተ ፡ መቅደሱ ፡ አስተዳዳሪ ፡ ሹም ፡ ከቤተ ፡ መቅደሱ ፡ ገንዘብ ፡ አደራጅቶ ፡ እንዲያስፈጽም ፡ ተወስኗል ።

www.ethiopianorthodox.org

የቤተ ፡ መቅደሱም ፡ አስተዳዳሪ ፡ ሹም ፡ ክርስትና ፡ የተነሱትንና ፡ የሞቱትን ፡ ሰዎች ፡ ስም ፡ ዝርዝር ፡ በ፫ ፡ በ፫ ፡ ወር ፡ በወረዳው ፡ ለሚገኘው ፡ የካህናት ፡ አስተዳዳሪ ፡ ሹም ፡ እንዲያስታውቅና ፡ የካህናት አስተዳዳሪ ፡ ሹምም ፡ በመን ፈቅ ፡ በመንፈቁ ፡ በየሀገረ ፡ ስብከቱ ፡ ላለው ፡ ጳጳስ ፡ ጽ/ቤት ፡ እንዲያስረክብ ፡ የሀገረ ፡ ስብከቱ ፡ ጳጳስ ፡ ጽሕ ፈት ፡ ቤትም ፡ በየዓመቱ ፡ መጨረሻ ፡ በነሐሴ ፡ ወር ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ በሚገኘው ፡ ለመንበረ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ ጠቅላላውን ፡ ዝርዝር ፡ እንዲያስተላ ልፍ ፡ ተወስኗል ።

፫ኛ ፡

## ስለ ፡ ውግዘት ፡ አኳኋን ።

ሰው ፡ ማውገዝ ፡ የሚገባው ፡ ሃይማኖቱን ፡ ሲክድ ፡ ሕገ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ሲያፈርስ ፡ አንድ ፡ ሁለት ፡ ጊዜ መክረውት ፡ የማይመለስ ፡ ሲሆን ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በከንቱ ፡ ማውገዝ ፡ አይገባም ። ማቴ፡ ም፡ ፲፰ ፡ ቍ፡ ፲፭ - ፲፯ ።

ካህን ፡ በማንኛውም ፡ ተርታ ፡ ነገር ፡ አውግዞ ፡ ቢገኝ ፡ ይቀጣል ።

ጨዋም ፡ ቢሆን ፡ ያወገዘው ፡ ሳይኖር ፡ በፈቃዱ ፡ የእገሌ ፡ ሥልጣን ፡ አይፍታኝ ፡ ማለት ፡ አይገባውም ፡ ቢልም ፡ የአፍ ፡ ስሕተት ፡ ወይም ፡ መሐላ ፡ ይባላል ፡ እንጂ ፡ የሕዝባዊ ፡ ቃል ፡ ውግዘት ፡ አይሆንም ። ቢሆ ንም ፡ ጥቂት ፡ ቀኖና ፡ ያስፈልገዋልና ፡ ቀኖናውን ፡ ከመ ምህረ ፡ ንስሐው ፡ ተቀብሎ ፡ መፈጸም ፡ አለበት ። ማቴ፡ ም፡ ፫ ፡ ቍ፡ ፴፬-፴፯ ።



፬ኛ ፡

## ስለ ፡ ሰባክያን ።

ሰባክያን በመንፈሳዊ ጉባኤ ሃይማኖታቸው ተመስ ክሮላቸው ፡ ትምህርታቸው ፡ ታውቆላቸው ፡ እንዲሰብኩና እንዲያስተምሩ ፡ የፈቃድ ወረቀት ይሰጣቸዋል ።

ሃይማኖታቸው ፡ ሳይመሰከርላቸው ፡ ትምህርታቸው ሳይታወቅላቸው ፡ ከየክፍሉ ጳጳሳት ፡ የሚያስተምሩበት የፈቃድ ፡ ወረቀት ሳይሰጣቸው ፡ እንዳይሰብኩ ተከልክሏል

ይህንም ፡ ደንብ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ኃላፊዎች የሆኑ ፡ ሹማምንት ፡ እንዲጠብቁ ፡ ተወስኗል ።

፭ኛ ፡

## ሕዝበ ፡ ክርስቲያን ፡ የንስሐ ፡ አስተዋፅዖ ፡ ማድረግ ፡ ስለሚገባቸው ።

ምዕመናን ፡ ሁሉ ፡ አሥራት ፡ በኵራት ፡ እያወጡ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ መርዳት ፡ ይገባቸዋል ፡ እንደሚገ ባም ፡ የሚያስረዳ ፡ በቅዱሳት ፡ መጻሕፍት ፡ ታዝዞ ፡ ይገኛል ። ኢሳይያስ ፡ ም፡ ፶፰ ፡ ቍ፡ ፲-፲፫ ፡ ሆሴዕ ፡ ም፡ ፲ ፡ ቍ፡ ፲፪ ፡ ማቴ፡ ም፡ ፳፪ ፡ ቍ፡ ፳፭ ፡ ቆሮ ፡ ም፡ ፲ ፡ ቍ፡ ፫-፱ ።

ስለዚህ ፡ ሕዝበ ፡ ክርስቲያን ፡ ሁሉ ፡ ሲወለዱ ፡ ክር ስትና ፡ ተነሥተው ፡ ሥጋውን ፡ ደሙን ፡ ተቀብለው ፡ ከእ ግዚአብሔር ፡ ልጅነት ፡ የሚያገኙበት ፡ በኃጢአትም ፡ ቢሰነክሉ ፡ በንስሓ ፡ ኃጢአታቸውን ፡ ለማስተሥረይ ፡ የሚችሉበት ፡ ቢሞቱ ፡ የሚቀበሩበት ፡ ስለሆነ ፡ ማንኛ

www.ethiopianorthodox.org

ቸውም ፡ ሕዝበ ፡ ክርስቲያን ፡ ሁሉ ፡ በግዴታ ፡ ሳይሆን ፡ በውዴታ ፡ በመምህረ ፡ ንስሓቸው ፡ መሪነት ፡ በመምህ ራን ፡ ስብከት ፡ በየበዓላቱና ፡ እሁድ፡እሁድ ፡ ከሚሠጡት ፡ የሙዳዬ ፡ ምጽዋት ፡ ገንዘብ ፡ በቀር ፍሬ ፡ ግብር ፡ ሆኖ ፡ በየዓመቱ ፡ አንድ ፡ አንድ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ብር ፡ እያወጡ ፡ ለአጥቢያው ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ መስጠት ፡ ይገባቸዋል ።

ይኸውም ፡ ገንዘብ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የምትተዳደርበትና ፡ የምትታደስበት ፡ የጐደለ ፡ ንዋየ ፡ ቅድሳት ፡ የሚሞላበት ፡ መጻሕፍት ፡ የሚገዙበት ፡ ሃይማኖታቸው ፡ የሚጠበቅበት ፡ ነውና ፡ ሕዝቡ ፡ በሚያምኑዋቸው ፡ በሁለት ፡ ሽማግሌዎ ችና ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ ምዕመናን ፡ በመረጡት ፡ ቄስ ፡ አማካይነት ፡ በሦስቱ ፡ ሰዎች ፡ ኃላፊነት ፡ እየተሰበሰበ ፡ እንዲቀመጥ ፡ ተወስኗል ።

## ፮ ኛ ፡

## ሥጋውን ፡ ደሙን ፡ ስለሚቀበሉ ፡ ሰዎች ።

ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ሥጋውን ፡ ቆርሶ ፡ ደሙን ፡ አፍስሶ ፡ የካሰ ፡ ለዓለም ፡ ሁሉ ፡ ቤዛ ፡ ሆኖ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ለጥቂት ፡ ሰዎች ፡ ብቻ ፡ አይደለም ።

ስለዚህ ፡ ክርስቲያን ፡ ለሆነ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ከሁሉ ፡ አስቀድሞ ፡ በሥጋ ፡ ወደሙ ፡ መወሰን ፡ ይገባዋል ።

ባልና ፡ ሚስት ፡ ሆነው ፡ በሥጋ ፡ ወደሙ ፡ ተወስ ነው ፡ ሲኖሩ ፡ አንደኛቸው ፡ በሞት ፡ ቢለዩ ፡ በሕይወት ፡ ሥጋ ፡ ያለው ፡ ንጹሕ ፡ ነኝ ፡ ሥጋውን ፡ ደሙን ፡ ለመቀ



በል ፡ ይገባኛል ፡ ብሎ፡ ከቀረበና ፡ መምህረ ፡ ንስሐው ም ፡ ከመሰከረለት ፡ ባይመነኵስም ፡ ሊቀበል ፡ ይችላል ።

## ፯ ኛ ፡

## በሐኪም ፡ ቤት ፡ ስላሉ ፡ ሕሙማን ።

ሕዝበ ፡ ክርስቲያን ፡ የሆኑ ፡ ሰዎች ፡ ታመው ፡ ወደ ፡ ሐኪም ፡ ቤት ፡ ሲገቡ ፡ መምህረ ፡ ንስሓቸው ፡ እስኪ ደርስላቸው ፡ ድረስ ፡ ጊዜ ፡ የማያገኙ ፡ ሆነው ፡ የሚናገዝገ ቄስ ፡ እንዳያጡ ፡ ሁልጊዜ ፡ የሚጎበኛቸውና ፡ የሚናገዘ ቸው ፡ ለየአንድ ፡ አንዱ ፡ ሐኪም ፡ ቤት ፡ አንድ ፡ አንድ ፡ ቄስ ፡ እንዲሰጥ ፡ ተወስኗል ።

ሥጋውን ፡ ደሙን ፡ ለመቀበል ፡ ቢፈልጉም ፡ ከዚ ያው ፡ ከሐኪም ፡ ቤት ፡ ሆነው ፡ ሊቀበሉ ፡ ይችላሉ ፡

## ፰ ኛ ፡

## በማዘት ፡ ቤት ፡ ስላሉ ፡ ሕዝበ ፡ ክርስቲያን ።

ማንም ፡ ሰው ፡ ቢሆን ፡ ለጊዜው ፡ መስሎትና ፡ ሰይ ጣን ፡ አነማሥቶት ፡ ሰውንና ፡ እግዚአብሔርን ፡ ቢበድል ፡ ቆይቶ ፡ በኃጢአቱ ፡ የማይጸጸት ፡ የለምና ፡ የንስሓ ፡ አባት ፡ በማጣት ፡ በኃጢአት ፡ ተሸፍኖ ፡ እንዳይሞት ፡ በየጊዜው ፡ ከእሥር ፡ ቤት ፡ እየገባ ፡ ሃይማኖትንና ፡ በጎ፡ ምግባርን፡ እያስተማረና፡ እያናዘዘ፡ የግዞተኞችን፡ ኃጢአት ፡ የሚያስተሠርይ ፡ ለእሥር ፡ ቤቶቹ ፡ ቄስ ፡ እንዲታዘዝ ፡ ተወስኗል ።

www.ethiopianorthodox.org

እስረኞችም ፡ ሕመም ፡ አግኝቷቸው ፡ ንስሓቸውን ፡ አድርሰው ፡ ሥጋውን ፡ ደሙን ፡ ለመቀበል ፡ የፈለጉ ፡ እንደሆነ ፡ ለእሥር ፡ ቤቱ ፡ ናዘዚ ፡ ቄስ ፡ አስታውቀው ፡ ንስሓ ፡ መግባታቸውንና ፡ ለሥጋው ፡ ደሙ ፡ መብቃታቸውን ፡ ቄሱ ፡ ከመሰከረላቸው ፡ ከእሥር ፡ ቤቱ ፡ በተለይ ፡ ንጹሕ ፡ ቦታ ፡ ተወስኖላቸው ፡ ሊቀበሉ ፡ ይገባቸዋል ።

## ፱ ኛ

## ስለሙታን ፡ ኀዘን ፡ ውሳኔ ።

ሕዝበ ፡ ክርስቲያን ፡ የሆኑ ፡ ሁሉ ፡ እናት ፡ አባት ፡ እህት ፡ ወንድም ፡ ልጅ ፡ ባል ሚስት ፡ እነዚህን ፡ የመሳሰለ ፡ ማንኛውም ፡ ዘመድ ፡ ወዳጅ ፡ በሞተባቸው ፡ ጊዜ ፡ እየዘለሉ ፡ ደረት ፡ እየደቁ ፡ ማልቀስ ፡ ሳይሆን ፡ በትእግሥት ፡ ሆኖ ፡ ማልቀስ ፡ ይገባል ፡ ተስፋ ፡ ትንሣኤ ፡ ተስፋ ፡ መንግሥት ፡ ሰማያትን ፡ እንደ ፡ ማያምኑ ፡ አሕዛብ ፡ ፊት እየነጩ ፡ ልብስ ፡ እየቀደዱ ፡ ደረት ፡ እየደቁ ፡ አልቃሽ ፡ እያቆሙ ፡ ሙሾ ፡ እያወጡ ፡ ማልቀስ ፡ ቀድሞ ፡ የተወገዘ ፡ ነውና ፡ አሁንም ፡ ፈጽሞ ፡ እንዲቀር ፡ ተወስኗል ።

ኀዘንተኞቹም ፡ ይህን ፡ ደንብ ፡ ሳይፈጽሙ ፡ ቢቀሩ ፡ ውግዘቱን ፡ በተላለፉበት ፡ ሕገ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ማፍረሳቸው ፡ ነውና ፡ የየደብሩ ፡ ሹም ፡ ሊቀጣቸው ፡ ይችላል ።



## ፲ ኛ

## ስለ ፡ ሕዝበ ፡ ክርስቲያን ፡ ፍትሐት

ክርስቲያን ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ሲሞት በመምህረ ፡ ንስሓው ፡ ኃላፊነት ፡ የዕለት ፡ ፍታቱን ፡ በአጥቢያው ፡ ያሉ ፡ ካህናት ፡ እንደሚገባው ፡ ይፈታሉ ፡ አስፈችውም ፡ ለካህናቱ ፡ ጥንት ፡ እንደቆየው ፡ እንደ ፡ ሀገሩ ፡ ልማድ ፡ የሚገባውን ፡ መስጠት ፡ አለበት ፡ ለፍታቱ ፡ የሚበቃ ፡ ገንዘብ ፡ የሌለው ፡ ቢሆን ፡ ግን ፡ ገንዘብ ፡ ማጣቱን ፡ የንስሓ ፡ አባቱ ፡ ከመሰከረለት ፡ ካህናቱ ፡ የዕለት ፡ ፍትሐቱን ፡ ያለዋጋ ፡ ሊፈቱ ፡ ይገባቸዋል ፡ ከሳልስት ፡ እስከ ፡ ዓመት ፡ ለማስፈታት ፡ ቢፈልግ ፡ ግን ፡ የሚገባውን ፡ እየሰጠ ፡ ማስፈታት ፡ ነው ።

በማንኛውም ፡ ምክንያት ፡ እግር ፡ አድርሶት ፡ መጥቶ ፡ በድንገት ፡ ሞቶ ፡ የተገኘ ፡ እንግዳ ፡ ግን ፡ ክርስቲያንነቱ ፡ ከታወቀ ፡ ያለዋጋ ፡ መፍታት ፡ ይገባል ።

## ፲፩ ኛ ፡

## ስለ ፡ መነኰሳት ፡ ሥርዓት ።

መነኰሳት ፡ የእንጦንስንና ፡ የመቃርስን ፡ ሕግ ፡ ተከትለው ፡ በፈቃዳቸው ፡ ራሳቸውን ፡ ለብሰዓት ፡ ሰጥተው ፡ ዓለምን ፡ ንቀው ፡ ከመነኰሱ ፡ በኋላ ፡ እንደገና ፡ ወደ

www.ethiopianorthodox.org

ዓለም ፡ ዞረው ፡ ሰብአ ፡ ዓለም ፡ በሚኖሩበት ፡ ከተማና፡ አገር ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ በፈቃዳቸው፡ እንዳይቀመጡ ፡ ተከልክሏል ።

ነገር፡ ግን ፡ ትምህርት፡ ለማስፋት ፡ ምሥጢር፡ ለማደላደል ፡ ከሉበት ፡ ገዳም ፡ የማይገኘውን ፡ ትምህርት ፡ ለመቀፀል ፡ ከአበ ፡ ምኔቱ ፡ ፈቃድ ፡ ተቀብለው ፡ የሚፈልጉትን፡ ትምህርት ፡ ወደሚያገኙበት ፡ የገዳም ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ቢሄዱ ፡ አይከለከሉም ።

በመነኰሱበትም ፡ ገዳም፡ በጎት፡ አጽንተው ፡ እየረዱ፡ ሲኖሩ ፡ ለመንፈሳዊ ፡ ሹመት ፡ የሚያበቃ ፡ ትሩፋት ፡ በመሥራታቸው፡ ሲመረጡ ፡ በደብርም ፡ በገጠርም ፡ ቢሆን ፡ ሊሾሙ ይችላሉ ።

ከሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ ከጳጳሳት ፡ ከኤጲስቆጶሳት ፡ ዘንድ፡ መንኰሰው ፡ እነዚሁ ፡ የመንፈሳውያን ፡ አባቶች ፡ ታዛዥዎች ፡ ሆነው ፡ ፈቃድ ፡ እየፈጸሙ ፡ እነርሱ ፡ ባሉበት ቦታ ፡ ተቀምጠው ፡ እየተማሩ ፡ የኖሩትም ፡ መነኰሳት፡ በእውቀታቸውና ፡ በደግነታቸው ፡ ለገዳም ፡ መምህርነትና፡ ለደብር ፡ አለቅነት ፡ ከዚያም ፡ በላይ ፡ ላለውና ፡ ለማንኛውም ፡ መንፈሳዊ ፡ ሹመት ፡ ቢመረጡ ፡ ሊሾሙ ፡ ይችላሉ ።

## ፲ ፬ ኛ ፤

## ምንኵስናን ፡ ስለሚፈልጉ ፡ ሰዎች ።

ምንኵስናን ፡ የሚፈልጉ ሰዎች ፡ ወንዶች ፡ ከወንድ ፡ ገዳም ፡ ሴቶች ፡ ከሴት ፡ ገዳም ፡ እየሄዱ ፡ ሕግ ፡ ምንኵስና፡



የተማሩ ፡ ገዳሙን ፡ እየረዱ ፡ ቆይተው ፡ እንደ ፡ መጽሐፈ መነኮሳቱ ፡ ትእዛዝ ፡ ባለፈው ፡ ተግሣፅ ፡ ለሚመጣው ፡ ምዕዳን ፡ ተቀብለው ፡ ሥርዓተ ፡ ምንኵስና ፡ ምን ፡ እንደሆነ ፡ ከተረዱ ፡ በኋላ ፡ ምንኵስና ፡ በፈቃድ ፡ የምትደረግ ፡ መሆኗን ፡ ዐውቀው ፡ እንችላለን ፡ ሲሉ ፡ መመንኰስ ፡ ይገባቸዋል ፡

ቄስ ፡ በሕግ ፡ ሲቀድስ ፡ ኖሮ ፡ ሚስቱ ፡ ብትሞት ፡ እስከ ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ ድረስ ፡ በሥልጣኑ ፡ ሲቀድስ ፡ ቆይቶ ፡ ከአንድ ፡ ዓመት ፡ በኋላ ፡ ከሀገረ ፡ ስብከቱ ፡ ጳጳስ ፡ ምንኵስና ፡ ተቀብሎ ፡ በክፍሉ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ተወስኖ ፡ በሥልጣኑ ፡ እያገለገለ ፡ ሊኖር ፡ ይችላል ።

በየደብሩና፡ በየገጠሩ ፡ የሚቀመጥ ፡ ፈቃድ ፡ የሌለው ፡ ማንም ፡ መነኵሴ ፡ ግን ፡ ቆሞስ ፡ ነኝ ፡ በማለት ፡ ምንኵስናን ፡ እንዳይሰጥ ፡ በፍጹም ፡ ተከልክሏል ። ሲመነኵስም ፡ አመንኳሹ ፡ ቆብ ፡ ብቻ ፡ መጫን ፡ ሳይሆን ፡ በምን ፡ ምክንያት ፡ ምንኵስና ፡ እንደፈለገ ፡ ጠይቆ ፡ ከመኰነሰ ፡ በኋላ ፡ ሊሠራው ፡ የሚገባውን ፡ ሁሉ ፡ ጸሎትን ፡ ስግደትን ፡ ተግባረ ፡ ዕድን ፡ አስተምሮ ፡ የሚኖርበትን ፡ ቦታ ፡ ገዳም ፡ ወስኖ ፡ ማመንኰስ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ መንኳሹ ፡ ቀርቦ ፡ የታዘዘውን ፡ ምዕዳንና ፡ ጸሎት ፡ ሳያደርስለት ፡ ቆብ ፡ እንዳይሰጠው ፡ ተወስኗል ።

በእርጅና ፡ ለደበመና ፡ ለታመመ ፡ ሰው ፡ ግን ፡ መንኳሹ ፡ ጉልበት ፡ አጥቶ ፡ ራሱ ፡ መጥቶ ፡ ምዕዳኑን ፡ ጸሎቱን ፡ ለመቀበል ፡ የማይችል ፡ ከሆነ ፡ አመንኳሹ ፡ ሄዶ ፡ ሥር

www.ethiopianorthodox.org

ዓቱን ፡ አድርሶ ፡ ከሕመሙ ፡ ሲድን ፡ ወደ ፡ ገዳም ፡ ሄዶ ፡ መቀመጥ ፡ የሚገባው ፡ መሆኑን ፡ አስረድቶ ፡ እንዲያ መነኩሰው ፡ ይፈቀዳል ፡

## ፲፫ኛ ፤

## መነኮሳት ፡ ወንጌልን ፡ ለመስበክ ፡ ካልሆነ ፡ በቀር ሹመትን ፡ እንዳይፈልጉ ፡ ስለመከልከላቸው ።

መንፈሳዊ ፡ ጉባኤ ፡ ለስብከተ ፡ ወንጌል ፡ ይፋጠ ናሉ ፡ ልበ ፡ ምእመናንን ፡ ያንፃሉ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ ያቀናሉ ፡ ብሎ ፡ ለመንፈሳዊ ፡ ሹመት ፡ አስበ ፡ ከበዓታ ቸው ፡ ለስብከተ ወንጌል ፡ ከሚልኳቸው ፡ በቀር ፡ በፈቃዳ ቸው ፡ ሰብአ ፡ ዓለም ፡ በሚኖሩበት ፡ ከተማና ፡ በየሀገር ፡ ቤት ፡ ውሥጥ ፡ እንዳይኖሩ ፡ ተከልክሏል ።

## ፲፬ኛ ፤

## የገዳማት ፡ መምህራን ፡ የደብር ፡ አለቆች ፡ የገጠር ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ ሹማምንትና ፡ አስተዳዳሪዎች ፡ በተሾሙበት ፡ በታ ፡ ጸንተው ፡ መኖርና ፡ ማስተማር ፡ ስለሚገባቸው ።

የገዳማት ፡ መምህራንና ፡ የአድባራት ፡ ካህናት ፡ የገጠር ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ አስተዳደር ፡ ሹሞች ፡ በተሾ ሙበት ፡ ሀገር ፡ ጸንተው ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ ማገል ገል ፡ ሕዝቡን ፡ መምከርና ፡ ማስተማር ፡ ይገባቸዋል ፡ እንጂ ፡ የተሾሙትን ፡ ገዳምና ፡ ደብር ፡ ትተው ፡ ከከ ተማ ፡ ተቀምጠው ፡ ወይም ፡ መኖሪያ ፡ ቤታቸውን ፡ በሌላ ፡ ሀገር ፡ አድርገው ፡ አበሉን ፡ በተሾሙበት ፡ ሀገር ፡ እየበሉ ፡ የተሾሙበትን ፡ ሀገር ፡ ትተው ፡




በየወደዱበት ፡ ሀገር ፡ መኖር ፡ ተከልክሏል ።

ከዛሬ፡ ጀምሮ፡ እንደዚህ ፡ ያለውን ፡ ኑሮ ፡ የሚፈልጉ ፡ ሰዎች ፡ ሹመታቸውን ፡ እንዲለቁ ፡ ተወስኗል ።

## ፲፭ኛ ፤

## ስለ ፡ ክህናት ፡ ልብስ ፡ ልዩነት ።

የመነኮሳትና ፡ የቀሳውስት ፡ የመዘምራን ፡ ልብስ ፡ ልዩ ፡ ሊሆን ፡ ይገባል ። መነኮሳት ፡ ኩቆብ ፡ በላይ ፡ ሻሽ ፡ እንዳይጠመጥሙ ፡ ተከልክሏል ።




የገዳም ፡ አበ ፡ ምኔቶችና ፡ የጳጳሳት ፡ እንደራሴዎች ፡ ቆብ ።

ለቆቡም ፡ አኳኋን ፡ ልኩ ፡ ተወስኗል ።

የጨዋ ፡ መነኮሴና ፡ የሴት ፡ መነኮሲት ፡ የሚያ ደርጉት ፡ ቆብ ፡ ስፌቱ ፡ አንስተኛ ፡ ሆኖ ፡ በራሳቸው ልክ ፡ አጭር ፡ ሊሆን ፡ ይገባል ።

www.ethiopianorthodox.org

ሥልጣነ ፡ ክህነት ፡ ያላቸው ፡ የመነኰሳት ፡ ቆብ ፡ እንደጥንቱ ፡ የስፌቱ ፡ ጣራ ፡ ሰብሰብ ፡ ያለ ፡ ሆኖ ፡ ጫፉ ፡ የተደፈነ ፡ እንዲሆንና ፡ በቁመቱና ፡ በስፌቱ ፡ ከፌሌዋ ፡ መነኰሴና ፡ ከሴት ፡ መነኰሲት ፡ የተለየ ፡ ሊሆን ፡ ይገባል ።



ሥልጣነ ፡ ክህነት ፡ ያላቸው ፡ የመነኰሳት ፡ ቆብ ።

ቀሳውስትም ፡ በራሳቸው ፡ ላይ ፡ የሚያደርጉት ፡ ምልክት ፡ ከክርቱን ፡ የተሠራ ፡ ሆኖ ፡ ጫፉ ፡ ፌሌርሶ ፡ ሳይደፈን ፡ ለምልክት ፡ ያህል ፡ ክፍት ፡ ሊኖረው ፡ ይገባል ።



ስለ ፡ ልብስም ፡ አኳኋን ፡ ሥልጣነ ፡ ክህነት ፡ ያላቸው ፡ መነኰሳት ፡ በውስጥ ፡ ጀለቢያ ፡ ወይም ፡ ቀፍጣን ፡ (እጀ ሰፊ ፡ ቀሚስ) ፡ ሆኖ ፡ ከላይ ፡ ኩብ ፡ ካባ ፡ እንዲደርቡ ፡ ተወስኗል ።

የካባው ፡ ፌሌርቅ ፡ አይነት ፡ እንደ ፡ ተገኘላቸው ፡ ሊለብሱ ፡ ይችላሉ ። የቀሳውስትም ፡ ልብስ ፡ እንደዚሁ ፡ እንደ ፡ መነኰሳቱ ፡ ልብስ ፡ አይነት ፡ ሊሆን ፡ ይገባል ።

የመዘምራንና ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አገልጋዮች ፡ ልብስም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ በሚያገለግሉበት ፡ ጊዜ ፡ ከሕዝባውያን ፡ የተለየ ፡ ሊሆን ፡ ይገባል ።

## ፪ ኛ ፡

## ስለ ፡ ቅዳሴ ፡ ልብስ ።

ቀሳውስት ፡ በቅዳሴ ፡ ጊዜ ፡ የሚለብሱት ፡ እጀ ፡ ሰፊ ፡ ቀሚስና ፡ እንደተለመደው ፡ ነጭ ፡ ካባ ፡ ላንቃ ፡ እንዲለብሱ ፡ በራሳቸውም ፡ ላይ ፡ በፊትና ፡ በኋላ ፡ አረንጓዴ ፡ መስቀል ፡ የተሰራበት ፡ ነጭ ፡ ቆብ ፡ ሊያደርጉ ፡ ይገባል ።

ዲያቆናት ፡ ንፍቀ ፡ ዲያቆናት ፡ አናጕንስጢሳውያን ፡ በቅዳሴ ፡ ጊዜ ፡ የሚለብሱት ፡ እጀ ፡ ሰፊ ፡ ቀሚስ ፡ በደ

www.ethiopianorthodox.org

ረቱና ፡ በጀርባው ፡ ትዕምርተ ፡ መስቀል ፡ ያለው ፡ እንዲሆንና ፡ በግራና ፡ በቀኝ ፡ ትከሻቸው ፡ ወርዶ ፡ በወገብ ፡ የሚተላለፍ ፡ መታጠቂያ ፡ ያለው ፡ (በድረሺን) ፡ እንዲሆን ፡ ይገባል ።

በእራሳቸውም ፡ ላይ ፡ በሚፉ ፡ መስቀል ፡ ያለበት ፡ ከፊሬርቅ ፡ የተሠራ ፡ አክሊል ፡ ሊያደርጉ ፡ ይገባል ።

ዲያቆን ሰሎሞን ዮሐንስ
0911860113
0111/271609
D.N Solomon Yohannes

www.ethiopianorthodox.org